



# የወላጆች መመርያ ለአዲስ የሜሪላንድ ግምገማዎች

በ2010፣ ሜሪላንድ Common Core State Standards (የጋራ ዋነኛ የስቴት መመዘኛዎች) (CCSS)ን ተቀበለች። CCSS፣ ተማሪዎች ከK–12ኛ በሚያደርጉት ጉዞ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነጥበብ (ELA) እና በሂሳብ ምን መማር እንደሚጠበቅባቸው፣ የፀና፣ ጥራት ያለው ግንዛቤ ይሰጣሉ።

በ2014-2015፣ ሜሪላንድ ከCCSS ጋር የተቀናጁ ግምገማዎች ማፍራት ትጀምራለች። አዲሶቹ ግምገማዎች ተማሪዎች መመዘኛዎቹን እንዴት በመወጣት ላይ እንዳሉ—እና፣ በመጨረሻም፣ በኮሌጅና በስራ እንዴት ስኬታማ እንደሚሆኑ—ለመለካት አገልግሎት ላይ እየዋሉ ነው።

## የጋራ ዋነኛ የስቴት መመዘኛዎች ምንድን ናቸው?

የጋራ ዋነኛ የስቴት መመዘኛዎች የተማሪን ትምህርት ለማበልፀግና ለማሻሻል የተተለሙ ናችው። CCSS ከቀድሞዎቹ መመዘኛዎች፣ ወጣት ሰዎችን ለኮሌጅና ለስራ የሚያስፈልጓቸውን እውቀትና ሙያዎች እየሰጡ፣ ለገሀዱ ዓለም ተፈላጊነት እና የበለጠ ግልፅነትና ፍፁምነት አላቸው። ጠንካራም ናቸው፣ የወደፊቱ የዩ.ኤስ. የሰራተኛ ሀይል በአለም አቀፍ ኤኮኖሚ መወዳደር የሚችል መሆኑን እያረጋገጡ።

አዲሶቹ መመዘኛዎች ከቀድሞ ባነሱ ጥቂት ርእሶች ላይ ያተኩራሉ እናም በሽምደዳ ክሂሎት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በፅንሰሀሳብና ሂሳዊ አስተሳሰብ ላይ፣ ያሰምራሉ። CCSS፣ ከክፍል ወደ ክፍል እውቀት እየገነባ ተማሪዎችን ወደሌሎች ከመሸጋገራቸው በፊት አስፈላጊ ፅንሰ ሀሳቦችን በቁጥጥራቸው ስር እንዲያደርጉ ያስችላል።

መመዘኛዎቹ ስርአተትምህርት አይደሉም። ስለስርአተትምህርት፣ መሳርያዎች፣ ቁሳቁሶች፣ እና መፃህፍትን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ተማሪዎቻቸውን ይበልጥ ለሚያውቁ ለአካባቢ የት/ቤት ስርአቶችና ት/ቤቶች ይተዋሉ።

CCSS፣ ከመምህራን፣ የት/ቤት አስተዳዳሪዎች፣ የኮሌጅ ፋከልቲ፣ ወላጆች፣ እና የትምህርት ባለሙያዎች ትብብር ያለው በአስተዳዳሪዎች (governors) እና በስቴት ት/ቤት የበላይ ተቆጣጣሪዎች የተመሩ፣ በስቴት የበላይ አነሳሽነት ነው የዳበሩት። በላቀ ሁኔታ በሁሉም ስቴቶች እስካሁን በተመሰረተው ላይ ይገነባሉ፣ በከፍተኛ ደረጃ በመፈፀም ላይ ከሚገኙ አገሮች ጋር በተስተካከለ ጥንካሬ መገኘታቸውን ለማረጋገጥም በአለም አቀፍ ደረጃ እርከን ላይ ተቀምጠዋል።

እስካሁን፣ 45 ስቴቶች እና የኮለምቢያ ዲስትሪክት CCSSን ተቀብለዋል።

በዚህ ፎል፣ ሜሪላንድ የCCSSን ለውጦች በያንዳንዱ ዲስትሪክት፣ የት/ቤት ስርአት፣ እና ት/ቤት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ አድርጋለች። ለዚህ ዝግጅት፣ ሜሪላንድ ባለፉት ሶስት ሰመሮች ስቴት ውስት ከሚገኙ ሁሉም 1,400 ት/ቤቶች የተወጣጡ የመምህራን ቡድኖች ያካተቱ ፕሮፌሽናላዊ የልማት ፕሮግራሞች አስተናግዳለች።

### መመርያው የሚያካትተው:-

- የተማሪን ብቃት ከይበልጥ ጠንካራ መመዘኛዎች አንፃር የሚለኩ አዲስ ግምገማዎች ድህረእይታ ማድረግ
- የፈተና ነጥቦች ናሙና ማድረግ/መውሰድ
- ለተማሪዎች፣ መምህራን፣ እና ለት/ቤቶች ተጠያቂነት ድህረ እይታ
- ለወላጆች ተጨማሪ መገልገያዎች

# ከCCSS-ጋር-የተቀናጁ ግምገማዎች

## ለምን አዳዲስ ግምገማዎች?

መምህራንና ርእሰመምህራን ባብዛኛው የተምሪዎችን አካዴሚያዊ ግኝት ለመለካት ስለሚያገለግለው ግምገማ ይናገራሉ። ይህ ሰነድ፣ የስቴት መመዘኛዎችን ለመቆጣጠር የት/ቤት ውጤታማነትና የተማሪን ግስጋሴ የሚለካ ፕሮግራም፣ የአመት መጨረሻ ሰሜቲቭ ግምገማን ገረፍ ገረፍ ያደርጋል። አገልግሎት ላይ የዋሉ ሌሎች ግምገማዎችን በሚመለከት፣ በሰተቀኝ ያለውን ሰንጠረዥ ተመልከቱ።

አዲሶቹ ማጠቃለያ (summative) ግምገማዎች በወላጆች፣ መምህራን፣ እና አሰሪዎች በወቅታዊ የስቴት ግምገማዎች ለረጅም ጊዜ ለነበሯቸው ቅሬታዎች መልስ ይሰጣሉ—በተለይም፣ ሂሳዊ አስተሳሰብንና እውቀትን የመተግበር ችሎታ ይልቅ፣ አውነታዎችን የማጥናት ችሎታን ይለካሉ።

የአካባቢ ት/ቤት ስርአቶች ትምህርትን ለማስታወቅ እና ለተማሪዎች ይበልጥ አመቻችተው ለማቅረብ መረጃዎችን በተለያዩ መንገዶች ይጠቀሙባቸዋል።

## አዲሶቹ ግምገማዎች ምን ልዩ ነገር አመጡ?

አዲሶቹ ግምገማዎች መምህራንን ስለ ተማሪዎች ከክፍል ወደ ክፍል ግስጋሴ ግንዛቤአቸውን ጥልቀት ለመስጠት ያግዛሉ—እናም በዚያው ልክ፣ በግስጋሴዎች ወስጥ ክፍተቶችን ለይተው ተማሪዎች ኮሌጅ ወይም የስራ ሀይል ከመግባታቸው እጅጉን አስቀድመው ትኩረት እንዲያደርጉባቸው።

| የግምገማ አይነቶች |
|---|
| በተወሰኑ መስኮች እውቀትንና ክሂሎቶችን ለመገምገም እንዳስፈላጊነቱ አመቱን በሙሉ በመምህራን የሚሰጡ ግላዊ ፈተናዎች። |
| ከጊዜ ወደ ጊዜ የተማሪን እድገት ለመለካት በተለዩ ወቅቶች ተደጋግሞ የሚሰጥ ተመሳሳይ ፈተና። |
| ከጋራ የመመዘኛዎች ስብስብ አንፃር የተማሪዎችን አፈፃፀም ለመለካት በስቴት የሚከናወኑ የአመት መጨረሻ ግምገማዎች።<br>ይህ ሰነድ የሰሜቲቭ ግምገማዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል። |

## የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነጥበባት ግምገማዎች የሚያሳዩት፡-

- ተማሪዎች የተለያየ ውስብስብነት ያላቸውን ፅሁፎች አንበበው ይገነዘቡ እንደሆነ
- የሚያሳምን መከራከርያ ለማድረግ ተማሪዎች ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን በሚገባ ያቀነባብሩ እንደሆነ
- የአካዴሚያዊ ቃላትን ትርጉም ለመወሰን ተማሪዎች በአውደ ንባብ ምን ያህል የመጠቀም ችሎታ እንዳላቸው

## የሂሳብ ግምገማዎች የሚያሳዩት፡-

- የቁጥር ትርጉም፣ አልጄብራዊ አስተሳሰብ፣ ጂዮሜትሪ፣ እና የአሀዞች ትንተና የሚያካትቱ አስፈለጊ የሂሳብ አስተሳሰቦችን ተማሪዎች ተገንዝበው መጠቀም ይችሉ እንደሆነ
- የተጨባጩን አለም ፕሮብሌሞች ለመፍታት ተማሪዎች የሂሳብ እውነታዎችን የመጠቀም ችሎታቸው መጠን
- ተማሪዎች የሂሳብ መከራከሪያዎች ለማድረግ  ያላቸው ጥንካሬ መጠን

National PTA

## የአዲሶቹ ግምገማዎች ጥቅሞች

- በሚመጡት ጥቂት አመቶች፣ ግምገማዎች ውጤቶችን በተጨማሪ ፍጥነት እና በቀላሉ ለማንበብና በቀላሉ ለመገንዘብ በሚያስችል ቅርፀት፣ እንዲሁም በመስመር ላይ፣ ያቀርባሉ። ወላጆች ይህን መረጃ ስለ ልጆቻቸው ግስጋሴ ከመምህራንና ከት/ቤት አስተዳዳሪዎች ጋር በበለጠ ለመገናኘት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፣ መምህራንም ትምህርትን ለልጆች ፍላጎት በይበልጥ በሚያመች ሁኔታ ለማቅረብ ያስችላቸዋል።
- በኮምፒውተር የተመሰረቱ ግምገማዎች የእርሳስና-የወረቀት ፈተናዎችን ይተካሉ (ቴክኖሎጂው የሌላቸውን ት/ቤቶች አይመልከትም)። በኮምፒውተር-የተመሰረቱ ግምገማዎች ይበልጥ ቀልጣፋ፣ ለፈጠራ ምቹ፣ እና ሳቢ/አስተናጋጅ ናቸው—እናም መምህራንና ወላጆችን የተማሪን ግስጋሴ ከተለያዩ ነጥቦች ይበልጥ ለመከታተል/ለመቆጣጠር ያስችሏቸዋል።
- አዲሶቹ ግምገማዎች ሜሪላንድን የተማሪን አፈፃጸም ከስቴት-አቀፍ ት/ቤቶችና ዲስትሪክቶች ጋር ብቻ ሳይሆን፣ CCSSን ከተቀበሉ ከሌሎች ስቴቶችም ጋር ማወዳደር ያስችላታል።
- የት/ቤት ዲስትሪክቶች ለወላጆች ውጤቶች ብቻ አይደለም የሚሰጧቸው፣ በአመቱ መጨረሻ የተመረጡ ጥያቄዎችና መልሶች ጭምር እንጂ፣ ወላጆችና መምህራን ተማሪዎች ምንና ምን መስኮች እንደተቆጣጠሩና በየትኛው እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ለመገንዘብ ያግዛቸው ዘንድ።
- አዲሶቹ ግምገማዎች፣ ስንክልና ያላቸውንና የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተመሪዎችን ጨምሮ፣ የሁሉን ተማሪዎች ግኙትና እድገት ትክክለኛ መለኪያዎች ለመስጠት የተተለሙ ናቸው። የመስመር ላይ ግምገማዎች ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች ክፍላቸው ከሚገኙ ሌሎች ጋር አንድ ላይ ፈተና እንዲወስዱ እያስቻሉ፣ የሚገጥሟቸውን የማየት፣ የመስማት፣ እና አካላዊ-የመንካት መጋረጃዎችንም ጥያቄ ትኩረት ያደርጉበታል። የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች የእንግሊዘኛ ብቃት ደረጃቸው የፈለገውን ቢሆንም በተለያዩ የይዘት መስኮች (ለምሳሌ፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ፣ እና ማህበራዊ ሳይንስ) እውቀታቸውን ለማሳየት ይችላሉ። አላማው ለነዚህ ተማሪዎች ጥቅም ለማትረፍ አይደለም፣ ወደ ትክክለኛ ውጤቶች ተፈላጊውን መዳረሻ ለማቅረብ እንጂ።

### አዲሶቹን ግምገማዎች ማን ነው የሚያዳብራቸው?

CCSS በስቴት-የተመራ ተነሳሽነት ስለሆነ፣ አብዛኛዎቹ አገር አቋርጠው የሚገኙ ስቴቶች በጋራ የስቴት ዋነኛ መመዘኛዎች በመመስረት አዳዲስ ግምገማዎች በማዳበር ከሚገኙ ከሁለት የስቴቶች ኮንሶርሺያዎች እንዱ ጋ መቀላቀል ይመርጣሉ። እነዚህም Smarter Balanced Assessment Consortium (ጮሌ የተመጣጠነ ግምገማ ኮንሶርሺየም) እና Partnership for Assessment of Readiness for College and Careers (ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁነት ግምገማ ሽርክና) (PARCC) ናቸው።

ሜሪላንድ ከሌሎች 18 ስቴቶች ተሪቶሪዎች ጋር በመሆን የPARCC አባል ናት። ቢሆንም፣ ሁሉም ግምገማዎችን የሚመለከት የማስተካከልና የመጨረሻ ውሳኔዎች፣ ከአካባቢ መምህራን ጋር በመሆን፣ በስቴት ደረጃ ይፈፀማል።

ስለPARCC በwww.parcconline.org ተጨማሪ ያንብቡ።

## የኮሌጅና የስራ ዝግጁነት ማብራርያ፡-

አንድ ተማሪ፣ ዲግሪ በሚያቀርብ በድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት-ባለው ኮርስ ወይም ለወደፊት እድገት እምቅ ችሎታ ባለው የስራ አቅጣጫ ለመግባት ተማሪዎችን በሚያስችል ከፍተኛ-ጥራት ያለው የሰርቲፊኬት ፕሮግራም፣ ተመዝገቦ ስኬታማ እንዲሆን—ያለምንም ማስተካከያ—የሚያስፈልገው የዝግጅት ደረጃ።

# የግምገማ ጥያቄዎች ናሙና፡-

**የሚከተሉት ጥያቄዎች በአዲሶቹ ግምገማዎች የሚገኙትን የሚወክሉ ናቸው። ለተጨማሪ ምሳሌዎች፣ www.parcconline.org/samples/item-task-prototypesን ጎብኙ።**

## የ4ኛ ክፍል የሂሳብ ጥያቄ ናሙና

ሶስት የLakeview School ክፍሎች ወደ መስክ ጉዞ በመሄድ ላይ ናቸው። ሰንጠረዡ፣ አስተማሪን ጨምሮ፣ በያንዳንዱ ክፍል የሚገኙ ሰዎች ቁጥር ያሳያል።

በአውቶቡሶች፣ በቫኖች፣ እና በመኪኖች ለመገልገል መምረጥ ይችላሉ።

| | የሰዎች ጠቅላላ ብዛት |
|---|---|
| የወ/ሮ ሩዊዝ (Mrs. Ruiz) ክፍል | 23 |
| የሚ/ር ያንግስ (Mr. Yangs) ክፍል | 25 |
| የወ/ሮ ኢቫን (Mrs. Evan) ክፍል | 24 |


አውቶቡሶች 20 መቀመጫዎች አሏቸው


ቫኖች 16 መቀመጫዎች አሏቸው


መኪኖች 5 መቀመጫዎች አሏቸው

በየትኞቹ ሶስት ስብጥሮች ሁሉንም ሶስቱን ክፍሎች ወደ መስክ ጉዞ ለመውሰድ መጠቀም ይቻላል።

- ◯ 1 አውቶቡስ እና 4 ቫኖች
- ◯ 1 አውቶቡስ እና 8 መኪኖች
- ◯ 3 ቫኖች እና 11 መኪኖች
- ◯ 2 አውቶቡሶች እና 3 ቫኖች እና 4 መኪኖች
- ◯ 1 አውቶቡስ እና 1 ቫን እና 6 መኪኖች

መልስ ገቢ አድርጉ

## የ6ኛ ክፍል እንግሊዘኛ ቋንቋ ሰነጥበብ ጥያቄ ናሙና

**ተማሪዎች አንድ ምንባብ ከ"Julie of the Wolves" በዣን ሲ. ጆርጅ እንዲያነቡና የሚከተሉትን እንዲመልሱ ይጠየቃሉ፡-**

**ናሙና ነገር**

ደራሲው በምንባቡ፣ ሚራክስ የምትባል ጠንካራ ገፀባህርይ አዳብሯል። ስለሚራክስ እና ገፀባህርይዋን ለመፍጠር ደራሲው ስለተጠቀመባቸው ዝርዝሮች አስቡ። ምንባቡ የሚያልቀው ሚራክስ ጥቁሩ ተኩላ እንዲመለከታት ስትጠብቅ ነው።

ምንባቡ ካለቀበት በመቀጠል አዲስ ታሪክ መፃፍ። በታሪካችሁ ላይ፣ በሚራክስ ለይ በቀጣይ ምን እንደሚደርስባት ስትነግሩ ስለሷ የተማራችሁበትን ተጠቀሙበት።

መልስ፡-

## የ10ኛ ክፍል የእንግሊዘኛ ስነጥበብ ጥያቄ ናሙና

**የናሙና ነገር**

"Daedalus and Icarus" በኦቪድ እና "To a Friend Whose Work Has Come to Triumph" በአን ሰክስተን በማንበብ የተማራችሁትን ሰክስተን ዳዴዎስንና ኢካሩስን እንዴት እንደለወጠቻቸው የሚተነትን መጣጥፍ ለመፃፍ ተጠቀሙባቸው።

ለመጀመር ያህል፣ ከሁለቱ ፅሁፎች ትኩረት የሚሰጠው፣ የጎደለ፣ ወይም የተለየን ለማገናዘብ፣ ነገር ግን ለትንተና የየራሳችሁን ትኩረት ለመስጠት ነፃነት እንዲሰማችሁ ትፈልጉ ይሆናል።

መጣጥፋችሁን ከሁለቱም ፅሁፎች የፅሁፍ ማስረጃ በመስጠት አዳብሩት። የመደበኛ እንግሊዘኛን ደንቦች መከተላችሁን አረጋግጡ።

መልስ፡-

## ወላጆች መጠባበቅ የሚችሉት

ይህ አዲስ የማርክ አሰጣጥ ዘዴ ያለው አዲስ ስርአት ነው። ስለዚህ፣ አዳዲስ ውጤቶችን ከቀድሞዎቹ ጋር በቀጥታ ማወዳደር አይቻልም።

አዲሶቹ ግምገማዎች፣ ፕሮብሌም አፈታት፣ አፃፃፍ፣ እና ሂሳዊ አስተሳሰብን የሚያካትቱ፣ ለተማሪዎች የወደፊቶች በተለይ አስፈላጊ ናቸው ተብለው የታመነባቸው ጥልቅ እውቀትና ክሂሎቶችን ይመዝናሉ። ውጤቶቹ ለተማሪዎች፣ ወላጆች፣ እና ለመምህራን፣ ተማሪዎች ለመመረቅ ገና ከመዘጋጀታቸው በፊት፣ ጉዳዮችን ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉ ችሎታ ይሰጧቸዋል።

### rigor ከፍተኛ ስለሆነ፣ የተማሪዎች የውጤት ግኝቶች መጀመርያ ላይ ዝቅተኛ ሊሆኑ ይችላሉ።

ዝቅ ማለት የተማሪ የመማር ችሎታ ወይም የትምህርት አፈፃፀም ማሽቆልቆል ነው ተብሎ የግድ መተርጎም የለበትም። መምህራን የአጭሩን-ጊዜ ማሽቆልቆል፣ አስተማሪዎችና ተማሪዎች ከመመዘኛዎቹ ጋር ይበልጥ እየተዋወቁ እና የሚያቀርቡትን ፈተናዎች ለመቋቋም ይበልጥ እየታጠቁ ሲሄዱ፣ እንደሚሻሻሉ ይጠብቃሉ።

### በሽግግር ወቅት ት/ቤቶች ተማሪዎችን እንዴት አድርገው ይደግፏቸዋል?

ት/ቤቶች ከመመዘኛዎች ጋር በትግል ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን ለማገዝ የተለያዩ ሞዴሎች ፈጥረዋል። የማስተካከያና የሰመር ኮርሶች፣ በክፍል-ውስጥ በተከናወኑ ግምገማዎች ተመስርቶ የክፍል-ውስጥ ማስተካከያዎች፣ እና ለይቶ በማውጣት ግላዊ ስልጠና መስጠት የአካባቢ የት/ቤት ስርአቶች ከሚጠቀሙባቸው የድጋፍ ስልቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

> *
> ወላጆች ስለ አዲሱ ስርአተ ትምህርት ለመማር እና የግምገማ ውጤት ዝቅተኛዎችን ለመቀነስ ልጆቻቸውን እንዴት እንደሚያግዙ ለመገንዘብ ከት/ቤት ወይም የዲስትሪክት የስርአተ ትምህርት ስራ መሪዎች ጋር አብረው መስራት ይችላሉ።

### የተማሪዎችና የመምህራን ተጠያቂነት እንዴት ተግባራዊ ይደረጋል?

የአካባቢ ፖሊስዎች/መመርያዎች በስቴት ግምገማዎች የብቃት ደረጃ ለማያሳዩ ተማሪዎች ወደኋላ ስለ የማስቀረትና ስለ የማስተካከል ይወስናሉ። ወለጆች ከት/ቤት ጋር በመተባበር ለልጃቸው ፍላጎት የተቀናጀ የማሻሻያ ፕላን ለማዳበር መስራት ይችላሉ።

የስቴት ግምገማ ውጤቶች ከሜሪላንድ መምህር ውጤታማነት ፕላን በርካታ ታሳቢዎች በተጨማሪ እንደ አንዱ ሆኖ ተካትተዋል። የተማሪ እድገት ውጤቶች በመምህር እና በርእሰመምህር በሁለቱም ግምገማ ላይ አገልግሎት ላይ ይውላሉ።

ሜሪላንድ የተማሪዎችን በስቴት ግምገምዎች ከአመት ወደ አመት እድገት የት/ቤት ግምገማዎችና የፌደራል ተጠያቂነት ለመወሰን ከቅድመ ሁኔታዎች አንዱ አድርጉ ያስበዋል።

> *
> እርምጃ ውሰዱ፡-
>
> ወላጆች ለልጆቻቸው በበለጠ ሊቆሙላቸው እንዲችሉ ተግባራዊ የሆነውን አዲሱን የተጠያቂነት ስርአት ጥብቅ ትኩረት ሊያደርጉበት ያስፈልጋቸዋል። ስኬትን ለማረጋገጥ ፈተና ከበቂ መገልገያዎች ጋር በሚገባ መተግበሩን ለማረጋገጥ የወላጆች ሀገራዊ ድምፅ ወሳኝ ነው። ሜሪላንድ ወላጆችንና መምህራንን በእምነት፣ ትብብር፣ እና በመከባበር በተመሰረቱ ሀሳባዊ ውይይቶች ማካተት አለባት። ተማሪዎች፣ መምህራን፣ እና ት/ቤቶች እንዴት ተጠያቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተጨማሪ ዝርዝሮች ከፈለጉ፣ ወይም በግምገማዎች ባጠቃላይ ተጨማሪ መረጃዎች ከፈለጉ፣ እባክዎን 410-767-0100 ይደውሉ። ልታቀርቧቸው የምትችሉ ጥቂት ጥያቄዎች እነሆ፡-
>
> - በአዲሶቹ ግምገማዎች ልጄ ብቃት ባያገኝ ምን ያስከትላል?
> - ተማሪዎች የብቃት ደረጃ ባያገኙ በመምህራን ግምገማ ላይ ምን አይነት ተፅእኖ ይኖረዋል።
> - በአዲሶቹ ግምገማዎች ውጤቶች የት/ቤት ደረጃ ምዘናዎች እንዴት ይለወጣሉ?

# ልጅዎን ማዘጋጀትና መደገፍ

- አዲሶቹን ፈተናዎች ከልጅዎ ጋር ተወያዩባቸው። ወደ አዲሶቹ ፈተናዎች ሲሄድ/ስትሄድ አለምፍራቱ(ቷ)ንና አለምረበሹ(ሿ)ን አረጋግጡ።
- ተለቅ ካለ/ች ልጅ ጋር፣ አዲሶቹ ግምገማዎች እሱ ወይም እሷ ከምረቃ በኋላ ለስኬት ተክክለኛ መንገድ ላይ መገኘቱ(ቷ)ን ለማረጋገጥ እና አንዳንድ ጉዳዮች ካሉ በጥዋቱ ለመለየትና ለነሱ ድጋፍ ለመስጠት የተፈጥሩ መሆናቸውን አብራሩ።
- ፈተናዎቹ መጀመርያ ላይ ፈታኝ መሆናቸውን ለልጅዎ ግለፁ። ከፍተኛ ተስፋዎች እንዳለዎትና በያንዳንዱ ደረጃ ለማገዝ ቦታው ላይ እንዳሉ ለልጅዎን ይንገሩ።
- የፈተና ውጤቶችን ከልጅዎ ጋር ሆነው ድህረ እይታ ያድርጉባቸው፣ ጠንካራ ጎን ያላቸውን መስኮችና ለመሻሻል ቦታ ያላቸውን ለመወያየት ገዜ እየወሰዱ። እንዳስፈላጊነቱ አስተማሪው(ዋ)ን የውይይቱ ተሳታፊ ያድርጉ።
- በቤት ውስጥ ለጥናት ፀጥታማ፣ ምቹ ቦታ ይስጡ ከፈተና በፊትም ልጅዎ ቆንጆ የእንቅልፍ ሌሊት ማግኘቱ(ቷ)ን ያረጋግጡ።

## በቂ ግንዛቤና ተሳትፎ ማድረግ

- ከጋራ የስቴት ዋነኛ መመዘኛዎች ጋር መልካም ትውውቅ ያድርጉ።
- የአዲስ ፈተና ጥያቄዎች ናሙናዎች ለመመልከትና ግምገማዎች እንዴት እንደዳበሩ ናሙናዎች ለማየት፣ ይህን ይጎብኙ፡- http://www.parcconline.org.
- በትምህርት ክፍል ትምህርቶችና ፈተናዎች አስተማሪ የሚፅፉቸውን ሁሉንም አስተያየቶች አንብቡ። አስተማሪዎችን ግልጽ ያልሆነ ነገር ካለ እንዲያብራሩ እና በአስተያየቶች ትኩረት ለመስጠት አብራችሁ እንዴት በላቀ ሁኔታ እንደምተስሩ ጠይቋቸው።
- የልጅዎን ግስጋሴ ይከታተሉ/ይቆጣጠሩ። ልጅዎ ተጨማሪ እርዳታ ካስፈለገው/ጋት ወይም ስለ አንድ ርእስ ይበልጥ ለመማር ከፈለገ/ች፣ ከአስተማሪው(ዋ) ጋር አብሮ በመስራት የግል ስልጠና፣ ከትምህርት ውጭ ክበቦች፣ ወይም የሌሎች መገልገያዎች እድሎችን ይለዩ።
- ፈተናዎች አንድ ልጅ ማድረግ የሚችለውን ፍፁም መለከኪያዎች አለመሆናቸውን ይገንዘቡ። ውጤቶች እሱ ወይም እሷ በፈተናው ቀን በነበረው/በነበራት ስሜት ወይም በመማርያ ክፍሉ የተለየ አቀማመጥ ተፅእኖ ሊነኩ ይችላሉ። ግመገማዎች ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ ነገር ግን የልጅን እድገት ለመወሰን ብቸኛ ታሳቢ ሊሆኑ አይችሉም።
- በልጅዎ ግስጋሴ ለመወያየት ከሱ ወይም ከሷ አስተማሪ ጋር በተቻለ መጠን ይገናኙ። ለፈተናዎች ለመዘጋጀት ለማገዝና የልጅዎን ብቃት ለማሻሻል ቤት ውስጥ ስለሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ይጠይቁ።

## ተጨማሪ መገልገያዎች

- CCSS በየክፍል ደረጃው ምን ትርጉም እንዳለው በዝርዝር ለመመልከት፣ ይህን ይጎብኙ፡- www.pta.org/parentsguide
- ስለ PARCC ኮንሰርሽም፣ ሜሪላንድ አባል የሆነችበት፣ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ ይህን ይጎብኙ፡- http://www.parcconline.org
- ስለሜሪላንድ ህዝባዊ ከK–12ኛ ክፍል ትምህርት መረጃ፣ www.MarylandPublicSchools.org ይጎንኙ

© Copyright 2013 National PTA. All rights reserved. መብቶች በህግ የተከበሩ ናቸው።
በMontgomery County Public Schools 0775.15 እንደገና የታተመ
ትርጉም በLanguage Assistance Services Unit • Division of ESOL/Bilingual Programs • Office of Curriculum and Instructional Programs • Amharic